የተመዘገበና ዋና መሥሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ የሆነ አክሲዮን ማኅበር ነው፤"

"፱/"የፋይናንስ ድርጅት" ማለት መድን ሰጪ ኩባንያ፣ ባንክ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኩባንያ፣ የጠለፋ መድን ሰጪ፣ አነስተኛ መድን ሰጪ፣ የፖስታ ቁጠባ ድርጅት፣ የሐዋላ ድርጅት፣ በዲጂታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት፣ ወይም በብሔራዊ ባንክ የሚወሰን ሌላ ተመሳሳይ ድርጅት ነው፤"

"፲፫/"ብድር" ወይም "ቅድሚያ ክፍያ" ማለት በተወሰነ ቀን ወይም ቀኖች ወይም በተጠየቀ ጊዜ በተለምዶ ከወለድ ጋር ተመልሶ እንዲከፈል ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ወይም ግዴታ በማስገባት በቀጥታ፣ ወይም እንዳልታቀደ ኦቨርድራፍት፣ ከሌላ አበዳሪ ጋር በትብብር በሚሰጥ ብድር እንደመሳተፍና ከሌላ አበዳሪ ብድር እንደመግዛት በመሳሰሉት በተዘዋዋሪ፣ ለማንኛውም ሰው ገንዘብ ከመስጠት ወይም ገንዘብ ለመስጠት ቃል ከመግባት የሚመነጭ ማንኛውም የአንድ ባንክ የፋይናንስ ሀብት ሲሆን ማናቸውም ባንክ ለማንኛውም ሰው በቀጥታ ወይም በስሙ ብድር ለመስጠት፣ ባንኩ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት አከራይ በሆነበት የሊዝ ፋይናንስ ስምምነት ማስረጃነት የይገባኛል መብትን ለ ማስተናገድና በተበዳሪው ስም የኦቨርድራፍት አገልግሎት ለመስጠት በውል ላይ ተመሥርቶ የተገባን ግዴታ ያጠቃልላል፤"

፫/ ከአዋጁ አንቀጽ ፪ (፲፱) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፳)፣ (፳፩)፣ (፳፪)፣ (፳፫)፣ (፳፬)፣ (፳፭) እና (፳፮) ተጨምረዋል፤



9/ "Financial Institution" means an insuranc company, a bank, a micro-finance institution, capital goods finance company, a reinsurer, micro insurance provider, a postal saving, money transfer institution, a digital financia service provider or such other similar institutior as determined by the National Bank;

13/"Loan" or "Advance" means any financial assets of a bank arising from a commitment to advance funds by a bank to a person that is conditioned on the obligation of the person to repay the funds, either on a specified date or dates or on demand, usually with interest, or from indirect advances such as unplanned overdrafts, participation in loan syndication and the purchase of loans from another lender; and includes a Contractual Obligation of a bank to advance funds to or on behalf of a person's claim evidenced by a lease financing transaction in line with Provisions of Relevant Law in which the Bank is the lessor, and an overdraft facility to be funded by a Bank on behalf of a person;

3/ A new sub-articles 20, 21, 22, 23, 24, 25 and 26 are added following to article 2(19) of the Proclamation:

/ የአዋጁ አንቀጽ ፫ (፩) ተሠርዞ በሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፩ ተተክቷል፤

"፩/ ማንኛውም ሰው ከብሔራዊ ባንክ የባንክ ሥራ ፈቃድ ወይም በዲጂታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት የመስጠት ፈቃድ ወይም ይሁንታ ሳያገኝ በኢትዮጵያ ውስጥ የባንክ ሥራ ማካሄድ ወይም በዲጂታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት አይችልም፡፡

/ የአዋጁ አንቀጽ ፫(፫) (ሰ) ተሠርዞ በሚከተለዉ አዲስ /ሰ/ ተተክቷል፡

"ሰ) የተሻሻለዉን የመመሥረቻ ጽሑፍ ወይም የመተዳደሪያ ደንብ ማስመዝገብ፡ ወይም"

/ ከአዋጁ አንቀጽ ፫ (፫) ቀጥሎ የሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተጨምሮ ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) ንዑስ አንቀጽ (፭) እና (፮) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡

"፬/ "በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም የአጭር ጊዜ ቁጠባን ለማሰባሰብ የሚደረግ ዘመቻ እና/ወይም ወደ ደንበኛው የሥራ ቦታ በመሄድ ጥሬ ገንዘብ የማሰባሰብን አገልግሎት በተመለከተ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ

/ የአዋጁ አንቀጽ ፱ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፱ ተተክቷል፡

4/ Article 3 (1) of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

"1/ No person shall transact banking business or provide digital financial services in Ethiopia without obtaining a banking business license or digital financial services license or authorization from the National Bank."

5/ Article 3 (3) (g) of the Proclamation is deleted and replaced by the following new paragraph (g):

"g) Register its amended Memorandum and Articles of Association; or"

6/ A new sub-article (4) is added following to (3) of Article 3 (3) of the Proclamation and the existing sub-articles (4) and (5) are renumbered as sub-articles (5) and (6) :

"4/ Notwithstanding paragraph (a) of sub-article (3) of this Article, the National Bank may issue a Directive on short time saving mobilization campaigns for a short period and/or cash collection services at customer's premises."

7/Article 9 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 9:

፳፮/በአዋጁ በተለያዩ ቦታዎች "ቁጥጥር/ የቁጥጥር ሥራ"፣ "ተቆጣጣሪ"፣ "ቁጥጥር እንዲያካሂዱ" እና "ቁጥጥሩ በተደረገበት" ተብለው የተጠቀሱት "የምርመራ ሥራ"፣ "መርማሪ" እና "የምርመራውን ሥራ እንዲያካሂዱ" እና "ምርመራው በተደረገበት" በሚሉት ተተክተዋል፡፡

**<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጳጉሜ ፬ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ሣህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት



26/The reference to the "inspectio ,"inspect", "inspector", and "inspected" i different part of the Proclamation are repeale and replaced by "examination", "examin "examiner", and "examined", respectively.

**3. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on the dat of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On the 9th Day of September, 2019**

**SHALEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**